Rift Valley Institute
MAKING LOCAL KNOWLEDGE WORK

Peace Research Facility

# የሐዋሳ ከተማ ውዝግቦችና ተለዋዋጭ ገፅታዎቻቸው


## ኢዮብ ባልቻ ገብረማርያም እና ሮቤል ሙላት


## ማጠቃለያ

- በኢትዮጵያ ከተሞች የሚታዩ ውዝግቦችን ማጥናት፣ ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉ የከተማ ማዕከላት የሚስተዋሉ ጉልህ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ለውጦች ምን ዓይነት መልክ እንዳላቸው ለመገንዘብ ይረዳል።
- በዚህ ረገድ በቅርቡ የተመሠረተው የሲዳማ ክልል ርዕሰ መዲና በሆነችው የቀድሞ የደቡብ ክልል ዋና ከተማ ሐዋሳ ላለፉት ሦስት አስርት ዓመታት ጎልተው የታዩ የተለያዩ ውዝግቦች ከክልል በታች ባሉ መዋቅሮች፥ በክልል እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ካስከተሏቸው ለውጦች አኳያ፥ ይህ ጥናት በሐዋሳ መደረጉ ምክንያታዊ ነው።
- ይህ ጥናት የውዝግቦቹን ተዋናዮች እና ሥፍራዎች በመለየት የውዝግቦቹን ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ማስረዳት ላይ ያተኮረ ነው።
- ሐዋሳን ማዕከል አድርጎ የሲዳማ ክልልን የመመሥረት ውዝግብ በደቡብ የሀገሪቱ ክፍል የነበረውን የክልል አደረጃጀት መልሶ ማዋቀርን በማነሳሳቱ የኢትዮጵያ የፌደራል አደረጃጀት ላይ በእጅጉ ተፅዕኖ አሳድሯል።
- ሐዋሳ የሲዳማ ክልል ልሂቃን የራሳቸውን ክልላዊ መንግሥት መመሥረት የሚችሉበትን አቅም እና የሲዳማን ማንነት የሚያስርግጡበት አደረጃጀትና እና ተቋማዊ የውይይት መድረክ ፈጥራለች።
- የሲዳማ ክልልን መመሥረት ተከትሎ ሌሎች ሦስት ክልሎች (ማለትም የማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች) ከቀድሞው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ራሳቸውን ችለው እንዲወጡ መንገድ ከፍቶላቸዋል።
- ጥናቱ፣ በተለያዩ ነገር ግን እርስ በእርስ በተያያዙ ሦስት ግኝቶች ላይ ትንታኔ በመስጠት የተዋቀረ ነው፡፡ በሦስቱ ግኝቶች መደራረብ መካከል ያለው ልዩነት ከተጨባጭነት ይልቅ ተተንታኝነት ያለው ሲሆን፣ ይህም በመሬት ላይ ያለው ሀቅ ውስብስብ እና እርስ በራሱ የተጠላለፈ መሆኑን የሚያሳይ ነው።
- የመጀመሪያው ጉዳይ የሲዳማ ክልልን ለመፍጠር የሲዳማ ልሒቃን ከፌደራል እና ከክልል መንግሥታት ጋር ያደረጉት ትግል ውስጥ ሐዋሳ ከተማን ለመቆጣጠር ያሳዩት ጥረት ላይ ያተኩራል። ይህም እንደ አቀባዊ (vertical) ውዝግብ ቀርቧል።
- ሁለተኛው ጉዳይ በሐዋሳ ውስጥ ባሉ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ እና ኃይማኖታዊ ቡድኖች መካከል በሚፈጠሩ ግጭቶች ላይ ያተኩራል። የሲዳማ እና የወላይታ ማኅበረሰቦችን እንወክላለን የሚሉ ልሂቃን፣ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እና የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ከተውጣጡ ቡድኖች ጋር ዋነኛ ተዋናዮች ተብለው ተለይተዋል። ጥናቱ ይህን እንደ አግድማዊ (የጐንዮሽ) ውዝግብ ያቀርባቸዋል።
- ሦስተኛው ደግሞ የቀድሞው ገዢ ፓርቲ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) በተግባር ላይ ለማዋል የሞከረው የልማታዊ መንግሥት ምሥረታ ሒደቶች በሐዋሳ ውስጥ ያለውን ውዝግብ በመቅረፅ ረገድ ያለውን የጐላ ሚና የሚያሳይ ነው። ይህ ንብርብር አዳዲስ ተዋናዮችን፣ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን እና ሂደቶችን ወደ ሐዋሳ በማምጣት፤ ከተማዋ በሲዳማ ልሂቃን፣ በደቡብ ክልል እና በፌደራል መንግሥት መካከል ቀጥተኛ የሽሚያ ማዕከል ማድረጉን የሚያሳይ ነው።

- ሐዋሳ በሲዳማ ምድር ላይ ስለመሆኗ የሲዳማ ልሂቃን ያነሱት ነጥብም በውዝግቡ ውስጥ ተለዋዋጭ ሁኔታን ፈጥሮ ነበር፡፡
- በአቀባዊ ውዝግቡ ውስጥ ዋነኛ ተዋንያኖቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሲሆኑ፣ የመከራከሪያ አምዶቻቸው ደግሞ በክልል እና በፌደራል መንግሥት ደረጃ የሚደረጉ እንደ ምርጫ፣ ሕዝበ ውሳኔ እና የውሳኔ አሰጣጥ ያሉ መደበኛ ሂደቶች ነበሩ፡፡
- በአቀባዊ ውዝግቡ ውስጥ አዎንታዊና አሉታዊ እርምጃዎች የተወሰዱ ሲሆን፣ እነርሱም ምርጫ መደገፍ፣ ማካካሻ መስጠት፣ ድምፅ አፈና እና ተቃውሞ ነበሩ፡፡
- በዋና ዋና ተዋናዮቹ መካከል በነበረው የኃይል ልዩነት አንዳንዶቹ አካሄዶች ከሌሎቹ ይልቅ ለውዝግቡ ሰፊ በር ከፍተዋል ፡፡
- አግድማዊ (የጎንዮሽ) ውዝግቡን ካባባሱ ምክንያቶች መካከል በተለያዩ ማኅበረሰቦች ውስጥ የነበረው የእኩልነት ጥያቄ፣ ረዥም ጊዜ የቆየው ሀብትን የመቆጣጠር እና ተደራሽነትን የማስፋት ፍላጐት እንዲሁም በብሔረሰብ ደረጃ ክልላዊ መንግሥት የመመሥረት ፕሮጀክት ተጠቃሽ ናቸው።
- ቋንቋ፣ የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች፣ ዋና ዋና መገናኛ ብዙሃን፣ ማኅበራዊ የትስስር ገፆች እንዲሁም እንደ ስፖርት እና ኃይማኖታዊ ክብረ በዓላት የጐንዮሽ ውዝግቦች በይበልጥ የሚከሰቱባቸው ስፍራዎች ናቸው ሲሆኑ፥ አመፅ የቀላቀለ የእርስ በርስ ግጭት፣ ማግለልን እንዲሁም ወሳኝ ሕዝባዊ ሥፍራዎችን የመቆጣጠር ፍልሚያን ያካተተ ነበር። የእርስ በርስ ግጭቱ በሕገ ወጥ መንገድ የተደራጁ ግለሰቦችንና ቡድኖችን አሳትፏል፡፡
- ኤጀቶ የተባለው የሲዳማ ወጣቶች ቡድን ሲዳማ ባልሆኑ – በተለይም በወላይታ ተወላጆች ላይ – ሲደርስ በነበረው ጥቃት ውስጥ ዋነኛ ተዋናይ ነበረ፡፡
- ሦስተኛው የውዝግቡ መንሥዔ የኢሕአዲግ ልማታዊ መንግሥት ለመመሥረት የወሰዳቸው የፖሊሲና የፖለቲካ ውሳኔዎች የተጫወቱት ሚና ነው፡፡ ይህ ልማታዊነት እንደ ሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ባሉ ዋነኛ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ውስጥ ይስተዋላል።
- በተያያዥነት የመጣው የከተማ መስፋፋት እንደ ፍልሰተኛ የጉልበት ሠራተኞች እና ድንበር ተሻጋሪ ድርጅቶች ያሉ አዳዲስ ተዋናዮችን ወደ ከተማዋ አምጥቷል፡፡ በመሆኑም ደመወዝ፣ መኖሪያ ቤት፣ መሬት እና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ላይ ጥያቄዎችን አስነስቷል፡፡
- የውዝግቡ መንስዔዎች ደካማ የከተማ እቅድ፣ ዝቅተኛ የአገልግሎት አሰጣጥ፣ በሙስና የተሞላ የመሬት ንግድ እና አያያዝ፣ የጉልበት ጭቆናና ብዝበዛን የመሳሰሉ በልማት ስራው ረገድ የተከሰቱ እምነት ማጣቶች ናቸው፡፡
- ነገር ግን ልማት የፈጠረውን ውዝግብ መረዳት ከአስተዳደራዊ ሁኔታዎች ባሻገር መመልከትንና እነዚህን የፖለቲካ ሂደቶች መመርመርን ይጠይቃል፡፡ ሆኖም የኢሕአዴግ ልማታዊነት ለሀገር ውስጥ ኩባንያዎች እና ለሠራተኞች ደኅንነትና መብት ትኩረት ከመስጠት ይልቅ የበለጠ ትኩረት ያደረገው የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ላይ ነበር፡፡
- በተመሳሳይ የኢሕአዴግ የኢኮኖሚ ዕድገት ስትራቴጂ የኢትዮጵያውያን ሠራተኞች ጉልበት በዓለም አቀፍ ካፒታል ስለመበዝበዙ ከመጨነቅ ይልቅ በአለም አቀፍ የጨርቃ ጨርቅ እና ልብስ አምራቾች የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ ላይ የበለጠ ትኩረት ነበረው፡፡

### የኢትዮጵያ የሰላም ምርምር ተቋም

ይህ ሪፖርት ለኢትዮጵያ የሰላም ምርምር ተቋም የተጻፈ ሲሆን፥ ውዝግብ የሚታይባቸው የከተማ ስፍራዎችን የተመለከቱ ጭብጦች የተዳሰሱበት የዕውቀት ለሰላም (Knowledge for Peace) ምርምሮች አካል ነው። የሰላም ምርምር ተቋም ገለልተኛ የሆነ ወቅታዊ የሰላምና የግጭት ትንታኔዎችን ከኢትዮጵያዊ ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች በማቀናጀት በአገሪቱ ግጭት አገናዛቢ የሆነ የፖሊሲና ፕሮግራም ቀረጻ እንዲኖር ያግዛል። ተቋሙ በሪፍት ቫሊ ኢንስቲትዩት (አር ቪ አይ) የሚተዳደር ሲሆን፥ በእንግሊዝ መንግሥት ድጋፍ ይደረግለታል።

### የስምጥ ሸለቆ የጥናት ተቋም

የስምጥ ሸለቆ የጥናት ተቋም በምስራቅና ማዕከላዊ አፍሪካ የሚሠራ ሲሆን፣ አገር በቀል ዕውቀቶች በማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። የቅጂ መብት © የስምጥ ሸለቆ የጥናት ተቋም 2017። ይህ ሪፖርት በክሪኤቲቭ ኮመንስ አሠራር መሠረት ለንግድ ሳልሆነ ዓላማ ይዘቱ ሳይቀየር መጠቀም እንዲቻል ተፈቅዶ የታተመ ነው (CC BY-NC-ND 4.0)።

Rift Valley Institute
MAKING LOCAL KNOWLEDGE WORK

Peace Research Facility